# ፈተና

ፈተና የሚለውን ቃል በጥቅሉ ስንመለከት ምናልባትም በአይምሮአችን ድቅን የሚለው ነገር ከትምህርት ጋር የተያያዘ የእውቀት መለኪያ ሆኖ የሚቀርበውን ፈተና ሊሆን ይችላል፤ፈተና ብዙ መልክና አቀራረብ አለው፡፤የተፈጥሮን ይዘትና ምንነት፣የህብረተሰብንና እንዲሁም የግለሰብን ማንነት አስተሳሰብና አቋም ለማወቅ፣የመድሃኒትን ፈዋሽነት ወይም መርዛምነት ለመረዳት የሚቀርቡ የመመርመሪያ መንገዶችና መመዘኛ ሕጎች አሉ።እነዚያም ሊታወቅ ለሚፈለገው ነገር ፈተናዎች ናቸው።

የሰው ልጅ እንደ ጤነኛ ሰው በግል ወይም በጋራ የማሰብና  የመስራት አቅምና ችሎታ እንዳለው ለማወቅና ለመረዳት የሚሰራውና የሚናገረው እንደፈተና ሆኖ ለሰውነቱ መመዘኛ ወይም የማንነቱ መግለጫ ሆኖ ያገለግላል።

ደግ ወይም ክፉ፣ጨካኝ ወይም እርህሩህ፣ፈሪ ወይም ጀግና፣ውሻታም ወይም ሃቀኛ፣አገር ወዳድ ወይም ከሃዲ፣ዘረኛ ወይም ሰብአዊ አመለካከት፣ፍቅርና ሰላም ወዳድነትና ጥላቻ አራጋቢነት፣በአጠቃላይ ስነምግባር የማንነት መግለጫ በመሆን ያገለግላሉ።እነዚህ የተዘረዘሩት መግለጫዎች የአንድ ሰው፣ ቡድንም ሆነ ማህበረሰብ ማንነት መለኪያ ሚዛኖች ወይም መፈተኛዎች ናቸው።

በበመዘኛው ሳጥን ውስጥ መግባትና አለመግባት የሚወሰነው ተመዛኙ በሚያሳየው አድራጎት ወይም ስነምግባር ነው።አንድ ባለጌ ወይም ጨዋ ሰው ለሚያሳየው ጸባይ የቅርብ ወይም የሩቅ ወገኑና ታዛቢ በአጋርነት ተመሳሳይ አስተሳሰብና አድራጎት ካሳዬ የዛ ህብረተሰብ ማንነት ከግለሰቡ አይለይም።ባለጌ ወይም ጨዋ ተብሎ ይደመደማል።

በጨዋነት ለመመዝገብና ፈተናውን ለማለፍ ያለው መንገድ በማህበረሰቡ ስም የሚረጨውን የጥላቻና  አጥፊ የባለጌ አመለካከት አለመቀበልና ማውገዝ ነው።ያንን አለማድረግ በሰውየው አድራጎት መስማማትና የሚያደርሰውንም አደጋ መቀበልና መደገፍ ይሆናል።

ከዚህ አጭር ትንተና በመነሳት ሰሞኑን ለትግራይ ተወላጆች በተለይ ለአጠቃላዩ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የቀረበ አንድ ፈተና አለ፤የምንነት ፈተና።ይኸውም በዚህ ሰሞን በትግራይ ሕዝብ ስም በአንድ ግለሰብ የተሰራጨ የአጥፍቶ መጥፋት ጥሪ የትግራይ ሕዝብ (ተወላጅ)እንዴት እንደሚያየው የሚጠይቅ ነው።

ለዚህ ጥያቄ የትግራይ ተወላጅ የሆነ ሁሉ በልዩልዩ ድርጅትም ስር የተሰለፈቢሆን(በህወሃት፣በታንድ፣በትግራይ ዴሞክራቲክ ንቅናቄ፣በአረና ትግራይ…ወዘተ) በግለሰቡ የቀረበውን አስተሳሰብ በመቀበል ወይም በማውገዝ ማንነቱን ማሳየትና ማረጋገጥ ይኖርበታል።ከግለሰቡ ጋር የማይስማማ ከሆነ በሕብረተሰቡ ስም ለረጨው መርዝ የሚገባውን ቅጣት በግለሰቡ ላይ ማስቀመጥ አለበት።

የትግራይ ማህበረሰብ በስሙ ለሚደረገው የዘር ማጥፋት ቅስቀሳ የኢትዮጵያን ሕዝብ በተለይም መርዝ የተነሰነሰበት የአማራ ማህበረሰብን ይቅርታ መጠየቅ ይኖርበታል።ያም ብቻ አይደለም እራሱን ከግለሰቡ ወይም ግለሰቡን ከትግራይ ማህበረሰብ መነጠል ይገባዋል።ይህ ለትግራይ ተወላጅ የቀረበ የማንነት ማረጋገጫ ፈተና ነው።

ፈተናውን ለማለፍ ወይም ለመውደቅ እያንዳንዱ የትግራይማህበረሰብ አባል በስብስብ፣በድርጅትም

ሆነ በግለሰብ ደረጃ ምርጫውን ይፋ ማድረግ ይኖርበታል።

ዛሬ በአማራው ላይ የተሰነዘረ የማጥፋት ዘመቻ፣ነገ እንደ አማራው ማህበረሰብ ለኢትዮጵያ አንድነትና ክብር ፣የጸረ አምባገነን ትግል በሚያካሂዱ ዜጎች በትግራይ ተወላጆች ጭምር ላይ ሊሰነዘር የሚችል
አደጋ እንደሚሆን ሊገነዘቡት ይገባል።

ሂትለር ከእሱ አስተሳሰብ የሚለዩትን ጀርመኖችንም እንዳልማረ ሁሉ እነሱንም ቢሆን የዚህ ስንኩል ሃሳብ ቅኝት እንደሚያጠፋቸው ማወቅ ይኖርባቸዋል። በዚህ ግለሰብ በኩል የተመዘዘው መሳሪያ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ ስለሆነ በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምን ዜጋ ሁሉ በዘረኞች ሊደርስበት የሚችለውን አደጋ አመላካች ማስረጃ ነው።

በተጨማሪም በ1997 .እ.ኢ.አ.(በ2005 ዓ.ም የአውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር)በቀድሞው የህወሃት መሪ በነበረው መለስ ዜናዊ የትግራይን ማህበረሰብ ከሌላው ነጥሎ የራሱ አጃቢ ለማድረግ በቅንጅት ዙሪያ የተሰለፈው ሕዝብ የትግራይን ተወላጆች ለመጨረስ ዕቅድ አለው በማለት ያናፈሰው የውሸት ውንጀላ እንደትምህርት ተወስዶ አሁንም በትግራዩና በሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል በተለይም በአማራውና በትግራዩ መካከል ቂምና ጥላቻ ለመፍጠር ታስቦ የተደረገ ቅስቀሳ ሊሆን ስለሚችል ሁሉም በየቤቱ ክትትልና ጥናት ማድረግ ይኖርበታል።

ግለሰቡ ተናገረው የተባለው የቪዲዮ ቅጅ መቼና በማን እንደተቀዳ፣የድምጽ መልእክቱ ሲቀዳ የግለሰቡ እንቅስቃሴ ተያይዞ ለምን እንዳልቀረበ፣እንዳልተቀረጸም ጥናትና ክትትል ያስፈልገዋል።

ለበለጠ ግንዛቤ በትግራይ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ(የእብደት ሳይንስ ቢባል ይሻላል)መምህር የሆነው በብዕር ስሙ ዘጽአትአናንይ በተባለ የትግራይ ተወላጅ ፣ የህወሃት አባልና ደጋፊ ግለሰብ የተሰራጨውን በአማራው ማህበረሰብ ላይ ያነጣጠረ የጥፋት ጥሪና ቅስቀሳ የሚያሳይ የቪዲዮ ቅጅ ተመልክታችሁ በቅድሚያ የትግራይ ተወላጆች የሆናችሁ ተገቢ መልስ ትሰጡበት ዘንድ አሳስባለሁ።

ከግለሰቡ ጋር መሆናችሁን ወይም አለመሆናችሁን ለቀረበላችሁ ፈተና የምትወስዱት እርምጃ ወሳኝ ነው ዝምታ የአብሮነት ምልክት ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ እንድታስቡት ይሁን።

**አገሬ አዲስ**